# ኪ ዳ ና ች ን
# KIDANACH'N

ልዩ ዕትም መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻፯ (፪ሺ፯) ዓመተ ምሕረት

Special Edition Meskerem 1, 2007 A.D
(September 11, 2014)

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥
ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና
የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን/ውያት የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡
በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"**
**to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

# የ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት፡
# ቀን መቍጠሪያ
## 2007 (2014-2015 Gregorian) Calendar

አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ።



ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

The Conquering Lion of the Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ

Ethiopia stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

# ልዑል እግዚአብሔር፡

ከዘመነ ማርቆስ ወደዘመነ ሉቃስ አሸጋግሮ፡
የኢትዮጵያን የነጻነት ህልውና በዓላችንን ፯፻፩፲፯ኛ ዓመት፥
የጌታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ፪፻፯ኛ ዓመት፡
እና
የእመቤታችን፡ የድንግል ማርያምን፡ ፪፻፩፲፳፫ኛ ዓመት፡
የልደታት በዓል፡ ለማክበር ለበቃንበት፡
ለአዲሱ፡ የ፪፻፯ (፳፲፯) ዓመተ ምሕረት፡
እንኳን አደረሰን!

\+ \+ \+

# <u>ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ</u>

፩ኛ፡ ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡ "ኢትዮጵያ፥ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. በታተመው መጽሓፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሓተታዎች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

፪ኛ፡ "በዘንዜከር" በተባለው፡ የየዕለቱ፡ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቁጥሮች ጋር የሚደመረው የ፳፻፯ ዓ. ም. ዓበቅቴ፡ ፲፩ (ዐሥራ አንድ)፥ መጥቅዑ፡ ፲፱ (ዐሥራ ዘጠኝ) መኾኑ ይታወቅ!

፫ኛ፡ በቀን መቁጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት ጻድቃንና ሰማዕታት፡ <u>ዕረፍታቸውን</u>፥ የአኀዞቹ የተለያዩት ቀለማት ደግሞ፡ የሚከተሉትን አብነቶች ያመለክታሉ፡-

(አ) ቀዩ፡ በእሑድ የቀጠለችውን ሰንበትን፥ ዓበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የፍስክ ዕለታት፥

(በ) አረንጓዴው፡ ንኡሳን በዓላትን፥

(ገ) ሰማያዊው፡ የሰባቱን አጽዋማት ቀኖች ያሳያሉ።

፬ኛ፡ መስከረም ፩ ቀን፡ አሮጌ የኾነውን ኹሉ ጥለን፥ ከየኹለንተናችን፡ በንስሓ አስወግደንና በመንፈስ ቅዱስ ታድሰን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፥ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደአዲስ ተሸላሚ ተቀብለን የምንጐናጸፍባትና የምንቀዳጅባት ዕለት ስለኾነች፥ ከዚህም ጋር፡ ለጌታችንና ለእመቤታችን የልደት በዓላት አክብሮት፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን ለማብቃት፡ ከአሮጌው፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ጳጒሜን፡ የንስሓ፥ እንደገሃድም ጾምና ንኡስ ሱባኤ አድርገን፡ በጾም በጸሎት አሳልፈናታል።

፭ኛ፡- በቀን መቍጠሪያው የየወሩ ሠንጠረዥ ግርጌ፡ ለየወሩ፡ ምንባቦች ተመድበዋል፡፡ እነዚህም የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን፥ እንዲሁም፡ በየሰንበቱ፥ በሌሎቹም የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ፡ ከቃለ እግዚአብሔር ዝክረ ነገር ላለመራቅ እንደሚቻል በመገመት ነው፡፡ መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም፡፡

፮ኛ፡- ጾሙና ጸሎቱ፥ የሱባኤው ጭምር፥ ምንባቡም፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም በኀብረት በመሰባሰብ ሊካኼድ ይቻላል፡፡

፯ኛ:- ይህን የቀን መቍጠሪያ፥ "አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" በሚል፡ ዓቢይ አርእስት ሥር፡ “አንደኛ መጽሐፍ”፡ ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ!"፥ “ኹለተኛ መጽሐፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውቀት ፍለጋ!" እና “ሦስተኛ መጽሐፍ: ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ!” ተብለው: ታትመው እየወጡ ያሉትን፥ እንዲሁም፡ በኢትዮጵያኛ እና በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ፡ «የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ ለኢትዮጵያ ሕፃናት፤ "አንደኛ እና ኹለተኛ መጻሕፍት"» የሚል አርእስት ያላቸውን ዕትሞች፥ ደግሞም፡ “ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት።" ከእነዚህ በቀር፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት” በሚል አጠቃላይ ርእስ ሥር: “አንደኛ መጽሐፍ”፥ “ኹለተኛ መጽሐፍ” እና “ሦስተኛ መጽሐፍ” ተብለው፥ በተከታታይ የወጡትን፥ እንዲሁም: ቀደም ብለው: “ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!”፥ “ኢትዮጵያ: የዓለሙ መፋረጃ!” እና Ethiopia: The Classic Case በሚሉ አርእስት: ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን፥ ሌሎችንም: ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት: የጎዋ ሰሌዳችንን መጎብኘት፥ እንዲሁም: ከዚህ በታች በተመለከቱት: ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች: መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።


**አሳታሚ እና አከፋፋይ**

Publisher & Distributor

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።**

**Ethiopia: The Kingdom of God**

መልእክት ሣጥን ቁጥር ፰፻፲፪ P. O. Box 812

ስልክና ዕምነቅ ቁ. 0፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና 0፲፩-፫-፳-00-፹፭ Tel. & Fax.

011-4-16-18-85 & 011-3-20-00-85

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ። Addis Abeba, ETHIOPIA

ወይም or

**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**

**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**

Email: info@ethkogserv.org

Web Site: www.ethkogserv.org


**+ + +**

# ፪ሺ፯ (፳፻፯ ) ዓመተ ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2014). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ: | | | | ፩ 11<br>የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ልደታት የኢትዮጵያ ነጻነት::<br>ኪዳነ አዳምና ሔዋን::<br>ራጉኤል ሊቀ መላእክት::<br>ቅዱስ ዮሓንስ መጥምቅ::<br>በርተሎሜዎስ: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ:: | ፪ 12<br>ዮሓንስ መጥምቅ | ፫ 13<br>አባ አንበስ ኢትዮጵያዊ |
| ፬ 14 | ፭ 15<br>ሄሮድስ የፈጃቸው ሕፃናት::<br>የአሕመድ ግራኝን ወረራ: በሃይማኖት ጽናት ተቋቁሞ የተጋደለ አጼ ልብነ ድንግል | ፮ 16<br>ኢሳይያስ ነቢይ | ፯ 17<br>ኢትዮጵያዊቷ ኤልሣቤጥ የመጥምቁ ዮሓንስ እናት።<br>መናኔ መንግሥት አጼ ተክለ ሃይማኖት | ፰ 18<br>ግዝረተ ኢየሱስ | ፱ 19 | ፲ 20<br>አጼ መስቀል::<br>(ግማደ መስቀሉ በ፲፩ኛው፻ ዓመት በ፩ኛ አጼ ዳዊት ወደኢትዮጵያ ስለገባ "አጼ መስቀል" ተባለ) |
| ፲፩ 21<br>አጼ በካፋ: ስመ ጥሩው ምሁር መሪ:: | ፲፪ 22<br>ስለንስጥሮስ ኑፋቄ የ፪፻ ሊቃውንት ጉባኤ በኤፌሶን | ፲፫ 23 | ፲፬ 24 | ፲፭ 25 | ፲፮ 26<br>ኪዳነ ኖኅ::<br>ደመራ<br>(ለመስቀል በዓል ዋዜማ: ለችቦ እሳት የዛፍ አጣኖችን መደማመር::) | ፲፯ 27<br>በዓለ መስቀል<br>ኢየሱስ ክርስቶስ የተሠዋበት እውነተኛው መስቀል የተገኘበት:: |
| ፲፰ 28<br>አባ ኤዎስጣቴዎስ ኢትዮጵያዊ: ስለቅዳሜ: ሰንበትነት የተከራከረ:: | ፲፱ 29 | ፳ 30 | ፳፩ 1<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ዕርገት::<br>የኢየሱስ ክርስቶስ ዜና መስቀል በግሼን ማርያም የሚነገርበት። | ፳፪ 2 | ፳፫ 3 | ፳፬ 4<br>ኪዳነ መልከ ጼዴቅ |
| ፳፭ 5<br>ዮናስ ነቢይ::<br>የክረምት (የዝናም) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 6<br>የመፀው (የጽጌ=የአበባ) ወራትና የጽጌ ማኅሌት መግቢያ። | ፳፯ 7 | ፳፰ 8<br>ኪዳነ አብርሃም | ፳፱ 9 | ፴ 10 | ማስታወሻ:- |

*"ወንዝም: ገነትን ያጠጣ ዘንድ: ከዔዶም እየወጣ ይፈስስ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ወገን ይከፈል ነበር:: ....... የወንዙ ኹለተኛ ወገን ስም: ግዮን ነው፤ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ኹሉ ይከብባል:: .......እግዚአብሔር አምላክም: ሰውን ወስዶ: ያበጃትም፥ ይጠብቃትም ዘንድ: በዔዶም ገነት አኖረው::"* ዘፍጥ. ፪፥ ፰-፲፯::

| | |
|---|---|
| የመስከረም ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘፍጥረት እና መጽሓፈ ጥበብ:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of T'q'mt (Oct.-Nov., 2014). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ 9 | ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 11 |
| ፪ 12<br>አባ ሕርያቆስ<br>የቅዳሴ ማርያም ደራሲ<br>የጽጌ ማኅሌት | ፫ 13 | ፬ 14<br>አብርሃ ወአጽብሓ<br>የቅዱሱ ኪዳን<br>ክርስትናን<br>በኢትዮጵያ<br>ያስፋፉ<br>ወንድማማች<br>ነገሥት። | ፭ 15 | ፮ 16<br>ሓና ነቢይት:<br>የነቢዩ<br>ሳሙኤል እናት:<br>አባ ጰንጠሌዎን<br>ከ፱ቱ ቅዱሳን<br>፩ዱ። | ፯ 17 | ፰ 18 |
| ፱ 19<br>አጼ ዳዊት:<br>የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን<br>ግማደ መስቀል<br>ከኢየሩሳሌም ያስመጣና<br>'ዓባይን እገድባለሁ' እያለ:<br>በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ክርስ<br>ቲያኖችን: ከእስላሞች<br>ጥቃት ያዳነ::<br>የጽጌ ማኅሌት | ፲ 20<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>በ፵ ቀኑ በእናቱ እቅፍ<br>ቤተ መቅደስ የገባበት::<br>በዓለ ስምዖን::<br>ሓና ነቢይት::<br>አጼ ፋሲል:<br>ካቶሊክነትን ተቃውሞ:<br>ተዋሕዶነትን ያጸና:: | ፲፩ 21<br>የሕፃኑ ኢየሱስና<br>የቅድስት እናቱ<br>ድንግል ማርያም<br>ስደት መታሰቢያ<br>እና<br>የጾሙ መግቢያ። | ፲፪ 22<br>ወንጌላዊው<br>ማቴዎስ: ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት ፩ዱ::<br>ቅዱስ ድሜጥሮስ:<br>የቀንና የዘመን<br>አቈጣጠርን<br>ያስተካከለ | ፲፫ 23 | ፲፬ 24<br>ፊልጶስ ሓዋርያ:<br>ኢትዮጵያዊዉን<br>ጃንደረባ<br>አቤሜሌክን<br>ያጠመቀ።<br>አባ ዘሚካኤል አቡነ<br>አረጋዊ: ከ፱ኙ<br>ቅዱሳን ፩ዱ::<br>ገብረ ክርስቶስ። | ፲፭ 25 |
| ፲፮ 26<br>የጽጌ ማኅሌት | ፲፯ 27<br>እስጢፋኖስ: ቀዳሚው<br>ሰማዕት:<br>የሹመቱ መታሰቢያ::<br>ዲዮስቆሮስ: የግብፅ ሊቀ<br>ካህናትና የተዋሕዶ<br>ሃይማኖት ተጋዳይ:: | ፲፰ 28 | ፲፱ 29<br>አጼ ይምራሕ:<br>ቀዳሚዎቹን የእስል<br>ምና ስደተኞች በኢ<br>ትዮጵያ አስተናግዶ<br>የሸኘውና እነርሱ:<br>"ነጋሽ" የሚሉት<br>ክርስቲያኑ<br>ኢትዮጵያዊ ንጉሥ | ፳ 30 | ፳፩ 31 | ፳፪ 1<br>ወንጌላዊው<br>ሉቃስ:: |
| ፳፫ 2<br>የጽጌ ማኅሌት<br>ፍጻሜ | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6<br>መድኃኔ ዓለም | ፳፰ 7<br>አማኑኤል::<br>አባ ይምዓታ:<br>ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፳፱ 8 |

*"እግዚአብሔር: ኖኅን አለው:-'የፈጠርሁትን ፍጥረት ኹሉ: ከሰው እስከእንስሳ፥ ከተንቀሳቃሽ እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ: ከምድር ገጽ አጠፋለሁና: አንተ: ቤተሰቦችህን ኹሉ ይዘህ: ወደመርከብ ግባ! በዚህ ትውልድ መካከል: በፊቴ: የእውነት ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና!' ኖኅም: እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ::..እግዚአብሔርም: በስተኋላው ዘጋበት:: የጥፋት ውኃም: በምድር ላይ: አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ዘነበ፤ ውኃውም በዛ፤ መርከቢቱንም አነሣ፤ እርሷም: በውኃው ላይ ተንሳፈፈች!"* የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው: ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉዞ: ቀይ ባሕርን አቋርጣ: አራራት ላይ ለማረፍ: ከኢትዮጵያ ተነሣች:: ዘፍጥ. ፯፥ ፩-፲፯::

| | |
|---|---|
| የጥቅምት ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሩት እና መጽሓፈ ሲራክ:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of H'dar (Nov.-Dec., 2014). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | ፩ 10<br>አጼ ነአኵቶ ለአብ፡ መንግሥቱን፡ በኢትዮጵያዊው የመልከ ጼዴቅ ሥርዓት የመራና ያስተዳደረ | ፪ 11 | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ 14<br>ለንጊኖስ፡ ጌታ፡ ተሰቅሎ ሣለ፡ ጎኑን በጦር የወጋና ኋላ አምኖ በሰማዕ ትነት የተጋደለ:: የስደት ጾም ማብቂያ። | ፮ 15<br>ቍስቋም፤ የሕፃኑ ኢየሱስ እና የቅድስት እናቱ የስደት መታሰቢያ በዓል |
| ፯ 16 | ፰ አርባዕቱ 17<br>እንስሳ። መንበረ ሥላሴን የሚሸከሙ ፬ቱ ሕያዋን ፍጡራን (ሰው፥ ላሕም፥ አንበሳና ንሥር) | ፱ 18<br>ስለአርዮስ ኑፋቄ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤ በኒቅያ | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>ቅድስት ሐና ኢትዮጵያዊት፡ የድንግል ማርያም እናት | ፲፪ 21<br>ሚካኤል ሊቀ መላእክት:: አጼ በእደማርያም ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፲፫ 22<br>አእላፍ መላእክት |
| ፲፬ 23<br>በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በደርግ የዓመፅና የክህደት ዘመን፡ የኢትዮጵያውያን እልቂት መነሻ። | ፲፭ 24 | ፲፮ 25<br>የጾመ ነቢያት መግቢያ | ፲፯ 26<br>አዲስ አበባ ከተማ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም. የተቈረቈረችበት | ፲፰ 27<br>ፊልጶስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፲፱ 28 | ፳ 29 |
| ፳፩ 30<br>ኪዳነ ሙሴ:: ሕፃን ማርያም፡በ፹ ቀኗ፡ በቤተ መቅደስ፡ በጌታ ፊት የቀረበችበት። ማርያም ጽዮን:: ማክዳ ንግሥትና ልጇ ምኒልክ | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>ቆርነሌዎስ ጻድቅ (የሓዋ. ምዕ. ፲) | ፳፬ 3<br>፳፬ቱ ካህናተ ሰማይ:: | ፳፭ 4<br>መርቆሬዎስ ሰማዕት | ፳፮ 5<br>በናግራን (የመን) የኢትዮጵያውያን ሰማዕታት:: በዚያ የአጼ ካሌብ ድል:: ኢየሱስ ሞዐ ዘሓይቅ:: | ፳፯ 6<br>አባ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ ዘደብረ ቍንጽል |
| ፳፰ 7<br>አባ ሊቃኖስ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፳፱ 8<br>የሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ቀሌምንጦስ:: የሰማዕታት መጨረሻ ጴጥሮስ | ፴ አጼ 9<br>ገብረመስቀል፤ በዘመኑ፡ የቅዱስ ያሬድ ሙያና የ፱ቱ ቅዱሳን ዜና የገነነበት:: የጾመ ነቢያት ማብቂያ | ማስታወሻ:- | | | |

*"...የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የኾነው መልከ ጼዴቅ፡ የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዓ በረከት ቁርባንን አዘጋጅቶ፡ አብራም፡ ጠላቶቹን ነገሥታት ወግቶ ሲመለስ፡ 'አብራም፡ ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ፡ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው' ብሎ ባረከው፤ አብራምም፡ ከኹሉ ሀብቱ፡ አሥራትን፡ ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው::"* **የእሥራኤላውያን አባት የኾነውን፡ አብርሃምን፡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የኢትዮጵያውያን አባት የኾነው፡ የኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው::** ዘፍጥ. ፲፬፥ ፲፯-፳::

| | |
|---|---|
| የኅዳር ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘፀአት እና ትንቢተ ኤርምያስ:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Tah'sas (Dec., 2014-Jan, 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 10<br>በዓለ ትስብእት፡<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>የተፀነሰበት።<br>ብሥራተ<br>ገብርኤል።<br>ኤልያስ ነቢይ።<br>ቤትሳባ<br>ኢትዮጵያዊት፡<br>የሰሎሞን እናት | ፪ 11<br>የጾመ ማርያም<br>መግቢያ | ፫ 12<br>ሕፃን ማርያም<br>በስዕለት፡ ለቤተ<br>መቅደስ የተሰጠችበት።<br>ፋኑኤል<br>ሊቀ መላእክት።<br>ዳግማዊ አጼ<br>ምኒልክ።<br>ሀብተ ጊዮርጊስ<br>አባ መላ። | ፬ 13<br>እንድርያስ፡<br>ከ፲፪ቱ<br>ሓዋርያት ፩ዱ |
| ፭ 14 | ፮ 15<br>በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም.<br>በፋሺስትጣልያን<br>የተሠየፉት<br>የአዲስ ዓለም<br>ማርያም<br>ሰማዕታት ካህናት | ፯ 16<br>ፅንሰታ<br>ለማርያም<br>(ድንግል ማርያም<br>የተፀነሰችበት) | ፰ 17<br>ኢትዮጵያዊው<br>አባ ኪሮስ | ፱ 18<br>አባ በአሚን፤<br>ኢትዮጵያዊ | ፲ 19<br>በወሎ፡ ደብረ<br>እግዚአብሔርና<br>የሓይቅ መካነ<br>እስጢፋኖስ፡ በኣሕመድ<br>ግራኝ ጦር<br>የተበዘበዙበት | ፲፩ 20 |
| ፲፪ 21<br>ስብከት።<br>ኢትዮጵያዊው<br>አባ ሳሙኤል፡<br>የዋልድባው | ፲፫ 22 | ፲፬ 23<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም<br>የፋሺስት<br>ጣልያን አየር<br>ኃይል በኢትዮጵያ<br>ላይ የመርዝ ጢስ<br>ማዝነብ<br>የጀመረበት | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰ 27<br>በአኵሱሙ<br>ሊቀ ካህናት<br>እንበረም ተልኮ፡<br>የግብፅን ጵጵስና<br>አገዛዝ<br>ወደኢትዮጵያ<br>ያመጣ አባ ሰላማ |
| ፲፱ 28<br>ብርሃን።<br>ቅዱስ ገብርኤል<br>፫ቱ ደቂቅን ከባቢሎን<br>እሳት ያዳነበት | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>ኪዳነ ዳዊት | ፳፬ 2<br>የእቲሳው<br>እጨጌ ተክለ<br>ሃይማኖት ልደት | ፳፭ 3<br>የመፀው<br>(የጽጌ) ወራት<br>ማብቂያ |
| ፳፮ 4<br>ኖላዊ።<br>የሓጋይ (የበጋ)<br>ወራት መግቢያ | ፳፯ 5<br>አጼ ኢያሱ<br>ብርሃን ሰገድ | ፳፰ 6<br>አማኑኤል | ፳፱ 7<br>በዓለ ወልድ | ፴ 8 | ማስታወሻ:- | |

*ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ ከባረከው በኋላ፡ እግዚአብሔር ተገልጦለት፡ "እኔ ኤልሻዳይ ነኝ! በፊቴ ተመላለስ! ፍጹምም ኹን! ቃል ኪዳኔን፡ በእኔና በአንተ መካከል አደርጋለሁ! እጅግም አበዛሃለሁ! ...ከዛሬ ጀምሮም፡ እንግዴህ፡ ስምህ 'አብራም' ተብሎ አይጠራ! ነገር ግን ስምህ፡ 'አብርሃም' ይኾናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና!" ያለው፡ ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው፡ ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ፡ ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን፡ በሚስትነት አግብቶ፡ ፡ "ምድያማውያን" የተባሉ ልጆችን በመውለዱ፡ ለኢትዮጵያዊነት አንዱ አብነት ኾኗል። ዘፍጥ. ፲፯፤ ፳፤ ፳፭።*

| | |
|---|---|
| የታኅሣሥ ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሳሙኤልና ትንቢተ ሕዝቅኤል። |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of TT'rr (Jan.-Feb., 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 9<br>እስጢፋኖስ: እንደ ጌታው: ለእውነት በደፋ መስከሮ የተ ሠዋ ቀናዒ ካህንና ቀዳሜ ሰማዕት | ፪ 10<br>አቤል ጻድቅ |
| ፫ 11<br>አባ መጣዕ (ሊባኖስ) ኢትዮጵያዊ | ፬ 12<br>ወንጌላዊው ዮሓንስ: ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፭ 13 | ፮ 14<br>ኖኅ፤<br>ዕርገተ ኤልያስ | ፯ 15<br>የአስተርእዮ ቅድስት ሥላሴ | ፰ 16 | ፱ 17 |
| ፲ 18<br>ከተራ: (ለጥምቀት በዓል ዋዜማ ውኃ: ከወንዝ ተወስዶ የሚከተርበት)::<br>የጾመ ማርያም ማብቂያ<br>(ጾመ ገሃድ) | ፲፩ 19<br>በዓለ አስተርእዮ ወጥምቀት::<br>ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ::<br>በቅዳሴ ጸሎቱ: የጥምቀት ወንዝ የቆመለት: የተጉለቱ ታቦት ዋሻ ካህን:<br>ትልቁ ወልደ ኢየሱስ | ፲፪ 20<br>ኢየሱስ ክርስቶስ: በቃና ዘገሊላ ሠርግ: በቅድስት እናቱ ፈቃድ የመጀመሪያ ተአምሩን ያሳየበት::<br>ሊቀ መላእክት ሚካኤል | ፲፫ 21<br>በ፴፬ ዓ.ም. በዘመኗ: በጃንደረባዋ አማካይነት: ክርስትና ወዳገርዋ የመጣላት: ሕንደኬ: ንግሥተ ኢትዮጵያ | ፲፬ 22<br>እንበረም: ሊቀ ካህ ናት ዘአኵስም: በ፫፻፴፫ ዓ.ም. የኢትዮጵያን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲሟላ ያደረገ | ፲፭ 23<br>ቂርቆስ: የ፫ ዓመት ሕፃን ሰማዕት | ፲፮ 24<br>ኢየሉጣ ሰማዒት: የሕፃኑ ቂርቆስ እናት |
| ፲፯ 25 | ፲፰ 26<br>ዝርወተ ዐፅሙ ለጊዮርጊስ | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት ወደገነት | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 |
| ፳፬ 1 | ፳፭ 2<br>የጾመ ኢትዮጵያ (ነነዌ) መግቢያ | ፳፮ 3 | ፳፯ 4<br>የጾመ ኢትዮጵያ ማብቂያ::<br>ዕርገተ ሄኖክ | ፳፰ 5 | ፳፱ 6 | ፴ 7 |

*ሙሴ: ከግብፅ: በስደት: ወደኢትዮጵያ መጥቶ: ስለኢትዮጵያዊነት: ከኢትዮጵያዊው ካህን: ከዮቶር ተምሮ ካመነ በኋላ: የካህኑን ሴት ልጅ: ሲጳራን አገባ፤ የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም: እነሆ: እግዚአብሔር ተገልጾለት: ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ: ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ: እውን ኾኗል:: ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም: የኋላ ኋላ: በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር: ከእሥራኤል ሕዝብ በደል እንደደረሰበት ተጽፏል:: ሙሴና የእሥራኤል ሕዝብ: ገና በምድረ በዳ ሠፍረው ሣሉ: የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን: ለእግዚአብሔር በማቅረብ: ሥርዓተ ክህነትን፥ ስለሕዝብ አስተዳደርና ፍትሕ አሰጣጥም በማስተማር: ሥርዓተ መንግሥትን: አማቱ ዮቶር: ለሙሴና ለአሮን፥ ለሕዝቡ ሽማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ: በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቧል:: ዘጸአ. ፫÷ ፩-፭፤ ፲፰÷ ፩-፳፯:: ዘኁል. ፲፪÷ ፩-፲፭::*

| | |
|---|---|
| የጥር ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ኢዮብ እና የማቴዎስ ወንጌል:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Yekkatit (Feb.-Mar., 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 8 ስለመቅዶንዮስ ኑፋቄ: የ፻፶ ሊቃውንት ጉባኤ በቍስጥንጥንያ። **መርዓዊ** | ፪ 9 | ፫ 10 የግሼን ማርያም አምባ: በ፲፭፻፳፬ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተመዘበረበት | ፬ 11 ጣይቱ ብጡል: ብርሃን ዘኢትዮጵያ | ፭ 12 | ፮ 13 ማርያም እንተ ዕፍረት: ጌታን: በሽቱ እና በእንባዋ እግሩን ያጠበችው | ፯ 14 |
| ፰ 15 **ዘወረደ** (ቅበላ) | ፱ 16 የጾመ ሕርቃልና የዓቢይ ጾም መግቢያ | ፲ 17 **ያዕቆብ ወልደእልፍዮስ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ** | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. ፋሺስት ጣልያን በሰላማውያን ኢትዮጵያውያን ላይ በአዲስ አበባ የፈጸመችው የግፍ እልቂት | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 |
| ፲፭ 22 **ቅድስት** | ፲፮ 23 **ኪዳነ ምሕረት** በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው:: የጌታ የአርባ ቀን ጾም መነሻ:: | ፲፯ 24 | ፲፰ 25 አዝማች ደገልሓን: የአሕመድ ግራኝን ጦር የተዋጋ ኢትዮጵያዊ ጀግና | ፲፱ 26 | ፳ 27 | ፳፩ 28 ከይሁዲቷ ጉዲት አገዛዝ በኋላ: በ፱፻፷፫ ዓ. ም. በአገዉ (በዛጔው) መርሓ ተክለ ሃይማኖት: ኢትዮጵያዊው የመልከ ጼዴቅ ሥርዓተ መንግሥት የተመለሰበት |
| ፳፪ 1 **ምኲራብ** | ፳፫ 2 ኢትዮጵያ: ኃይሏ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት የአድዋ ድል:: | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 | ፳፯ 6 አሕመድ ግራኝ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም ድል የኾነበት | ፳፰ 7 |
| ፳፱ 8 **መጻጕዕ** | ፴ 9 | ማስታወሻ:- | | | | |

*"ይሁዳ: የአንበሳ ደቦል ነው፤ ያስነሣውስ ዘንድ ማን ይችላል? ገዥ የኾነው እስኪመጣ ድረስ: በትረ መንግሥት ከይሁዳ፥ የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል አይጠፋም:: የአሕዛብም መታዘዝ ለእርሱ ይኾናል::" ..."በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው: በቀኝ እጁ ያለውን መጽሓፍ ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ: እጅግ አለቀስሁ፤ ከሃያ አራቱ አለቆች አንዱ: 'ኢትብኪ! ናሁ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ': ማለትም: 'አታልቅስ! እነሆ፥ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ: እርሱም የዳዊት ሥር: መጽሓፉን ይዘረጋ ዘንድ፥ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቷል!' አለ፤"* የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል: ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ተቀብለው: በምግባር ስለፈጸሙት: እውነተኞቹ እስራኤል: እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል:: ዘፍጥ. ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፥ ፩-፭::

| | |
|---|---|
| የየካቲት ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘዳግም፥ ትንቢተ ዮናስና የማርቆስ ወንጌል:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Meggabit (Mar.-Apr., 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | ፩ 10<br>አጼ ዮሓንስ ፬ኛ፡ የመተማው ሰማዕት፡ በእስላም ወራሪ የተሠየፈ | ፪ 11 | ፫ 12 | ፬ 13 | ፭ 14<br>ገብረ መንፈስ ቅዱስ |
| ፮ 15<br>ደብረ ዘይት | ፯ 16 | ፰ 17<br>ማትያን፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፱ 18 | ፲ 19 | ፲፩ 20<br>አባ አሌፍ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፩ዱ | ፲፪ 21 |
| ፲፫ 22<br>ገብር ኄር | ፲፬ 23 | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 | ፲፯ 26 | ፲፰ 27 | ፲፱ 28 |
| ፳ 29<br>ኒቆዲሞስ። | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>ዳንኤል ነቢይ | ፳፬ 2<br>ንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ | ፳፭ 3<br>የሓጋይ (የበጋ) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የጸደይ (የበልግ) ወራት መግቢያ |
| ፳፯ 5<br>**ሆሣዕና**<br>አጼ ገላውዴዎስ፡ ካቶሊካውያንን፡ በተዋሕዶነት የተቋቋመና በእስላም ወራሪ ሰማዕትነትን የተቀበለ | ፳፰ 6<br>የሰሙነ ሕማማት መግቢያ፡፡ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ፡ ስለሃይማኖትና ስለፍትሓ ነገሥት ዝግጅት፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤን፡ በኒቅያ ያሰባሰበ | ፳፱ 7 | ፴ 8 | ማስታወሻ፡- | | |

*"እነሆ፥ ለዳዊት፡ ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፡፡ እርሱም እንደንጉሥ ይነግሣል፤ ይከናወንለታልም፤ በምድርም፡ ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል፡፡...በዘመኑ እውነት ታብባለች፤ ሰላምም ይበዛል፡፡ ከባሕር እስከባሕር ድረስ፥ ከወንዝም እስከምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል፡፡ በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ፡፡ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ፡፡"..."እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ፡፡ አንተ፡ የእባቦችን ራስ፡ በውኃ ውስጥ ሰበርህ! የዘንዶውንም ራሶች ቀጠቀጥህ! ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው!"* ኤር. ፳፫፥ ፭-፮፤ መዝ. ፸፩፥ ፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬፡፡

| | |
|---|---|
| የመጋቢት ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ ኢሳይያስ እና የጳውሎስ መልእክታት፡፡ |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሚያዝያ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Miazia (Apr.-May, 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | ፩ 9 ጸሎተ ሓሙስ | ፪ 10 ስቅለት | ፫ ጌታ 11 በመቃብር ያረፈባት ሰንበት |
| ፬ 12 በዓለ ትንሣኤ | ፭ 13 ማዕዶት (በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ በመንፈስ፡ ወደትንሣኤ ሕይ ወት መሻገር፡፡) ሕዝቅኤል ነቢይ | ፮ 14 አርበኛው መሪ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ | ፯ 15 ኢትዮጵያዊው ኢያቄም፡ የድንግል ማርያም አባት | ፰ 16 አዳም ሓሙስ (የ፰ሺ፭፻ው ዓመተ ተስፋ ፍጻሜ ዝክር) | ፱ 17 | ፲ 18 |
| ፲፩ 19 ዳግም ትንሣኤ (ከፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ በኋላ ያለው የፍጻሜ ትንሣኤ መታሰቢያ) | ፲፪ 20 ደብረ ብርሃን፡ በ፲፭፻፴፫ ዓ. ም. በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት | ፲፫ 21 በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ፋሺስት ጣልያን ማኅበረ ሥላሴን፡ በአየር ኃይሉ የደበደበበት | ፲፬ 22 | ፲፭ 23 በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ሦስት የማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኰሳት፡ በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ |
| ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29 እጨጌ ዕንባቆም፡ ሰባኬሃይማኖት ሓዋርያ | ፳፪ 30 | ፳፫ 1 ጊዮርጊስ ሰማዕት | ፳፬ 2 |
| ፳፭ 3 | ፳፮ 4 | ፳፯ 5 ኢትዮጵያ፡ በፋሺስት ጣልያን ላይ በተቀዳጀችው ድል፡ ነጻነቷ የሚጠበ ቀው በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት | ፳፰ 6 ርክበ ካህናት | ፳፱ 7 | ፴ 8 ማርቆስ ወንጌላዊ | ማስታወሻ:- |

*የሳባ ንግሥት፡ በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን፡ የሰሎሞንን፡ ዝናውን በሰማች ጊዜ፡ ስለሃይማኖቱና ስለእውነተኛ ማንነቱ፡ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ፡ ከታላቅ ጓዝ ጋር ከአገርዋ ከኢትዮጵያ ተነሥታ፡ ወደኢየሩሳሌም መጣች፡፡ ለንጉሡም፡ መቶ ሃያ መክሊተ ወርቅ፥ እጅግም ብዙ ሽቱ፥ የከበረም ዕንቍ ሰጠችው፤ የሳባ ንግሥት፡ የሰጠችውን የመሰለ የስጦታ ብዛት፡ ከዚያ ወዲያ አልመጣም፡፡ የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከእርሱ ምልክትን ለሚጠይቅ፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ዘማዊም ትውልድ፡ እንዲህ የሚል፡ የመጨረሻ መልስን ሰጠ፡- ንግሥተ ዓዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፋረዳለች፥ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና፤ እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ! ከዚህ ፍርድ ለመዳን፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ዘርግታ ከምትኖረው፡ ከኢትዮጵያ ጋር፡ የምድር መንግሥታት መሪዎች ኹሉ፡ ለእግዚአብሔር ተቀኙ! ዘምሩም!*

፩ኛ ነገ. ፲፥ ፩-፲፤ ማቴ. ፲፪፥ ፴፪፤ መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፪፡፡

| | |
|---|---|
| የሚያዝያ ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ ዳንኤልና ራእየ ዮሓንስ፡፡ |

# ፪ሺ፯ (፳፪፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of G'nbot (May-June, 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሐሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ 7 | ማስታወሻ:- | | | | | ፩ 9<br>ቅድስት ድንግል ማርያም በሊባኖስ ተራራ የመወለዷ መታሰቢያ |
| ፪ 10<br>ኢዮብ ጻድቅ: ኢትዮጵያዊ | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13<br>ኢትዮጵያውያኑ ኤርምያስ ነቢይ፥ ደቀ መዛሙርቱ አቤሜሌክና ባሮክ | ፮ 14<br>የደብረ ሊባኖሷ ቅድስት ሰሎሜ ኢትዮጵያዊት | ፯ 15 | ፰ 16 |
| ፱ 17<br>ዕሌኒ ንግሥት: የጌታን መስቀል አስቆፍራ ያስገኘች | ፲ 18<br>በሃይማኖታቸው ጽናትከባቢሎን እሳት የዳኑት አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል | ፲፩ 19<br>ያሬድ: ኢትዮጵያዊው ማኅሌታይ ካህን::<br>አባ አሴር: የባሌ መምህር | ፲፪ 20<br>አጼ እስክንድር: የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል: ሰማዕትነትን: በወጣትነቱ የተቀበለ:: ዮሓንስ አፈወርቅ | ፲፫ 21<br>**ዕርገት**<br>የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኰሳት በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፬ 22 | ፲፭ 23<br>ናትናኤል: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ |
| ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27<br>ኢትዮጵያዊው አቡነ እግዚእ | ፳ 28<br>ቅዱስ አጼ ካሌብ ወደናግራን (የመን) ግዛቱ: በመርከብ ዘምቶ: አይሁዳዊዉን ወራሪ ጠላት: ድል ያደረገው | ፳፩ 29<br>የደርግ የክህደትና የዓመፅ አገዛዝ: በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. የተወገደበት | ፳፪ 30 |
| ፳፫ 31<br>**በዓለ መንፈስ ቅዱስ**<br>(በዓለ ፶) | ፳፬ 1<br>ዕንባቆም ነቢይ::<br>የሓዋርያት ጾም መግቢያ | ፳፭ 2<br>ቅድስት ሰሎሜ: በሕፃኑ ኢየሱስና እናቱ ስደት ያልተለየች | ፳፮ 3<br>የጾመ ድኅነት (የረቡዕና ዓርብ ጾም) መነሻ።<br>ቶማስ: ከ፲፪ቱ ሓዋርያት ፩ዱ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>አባ አፍጼ፣ አባ ጉባ፣ ከ፱ኙ ቅዱሳን ፪ቱ |

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር: ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ: "ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ: መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" አላቸው:: ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል: ቀድሞ: በሙሴ ላይ የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው: በኢትዮጵያዊት ሚስቱ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ: አሁን ደግሞ በእርሱ: በኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ ማስተዋል ነው:: "'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ: ለእኔ: እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።' ይላል እግዚአብሔር!"* ሲል: ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃል: በዚያን ጊዜም አላስተዋሉትም:: ዮሓ ፯፥ ፲፬-፳፬፣ ዘኍል. ፲፪፥ ፩-፲፮፣ አሞ. ፱፥ ፯::

| | |
|---|---|
| የግንቦት ወር ምንባብ:- | መጻሕፍተ አስቴር፥ ምሳሌና መክብብ:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Seney (June-July, 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ 8<br>ወንድሞቹ የሸጡት የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍና ኢትዮጵያዊት ሚስቱ አስናት | ፪ 9 | ፫ 10 | ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ 13<br>በፋሺስት ጣልያን የተመራ የራያ እስላም፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. የሸዋ ቆላ ኢትዮጵያውያንን በሰለባ የፈጀበት። |
| ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16<br>ሳሙኤል ነቢይ | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19<br>ሚካኤል ሊቀ መላእክት።<br>አጼ ላልይበላል | ፲፫ 20 |
| ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>አባ ገሪማ፡ ከ፱ቱ ቅዱሳን አንዱ። | ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ ሕንጸታ፡ 27<br>በአዳምና ሔዋን ኪዳኑ ሰብሳብ፡ በኢትዮጵያ የተመሠረተችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ኪዳነ ምሕረት፡ ኢየሩሳሌም ተፈጸመች።<br>ኤልሳዕ ነቢይ |
| ፳፩ 28<br>በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና ዓመፅ የፈጸመውን የኢትዮጵያ ትውልድ ሊቀጣ የተላከው ግፈኛው ደርግ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. የተቋቋመበት | ፳፪ 29 | ፳፫ 30<br>ንጉሥ ሰሎሞን፡ የምኒልክ አባት | ፳፬ 1<br>ሙሴ (ጸሊም) ኢትዮጵያዊ | ፳፭ 2<br>ያስቆሮቱ ያይደለ፡ ሓዋርያው ይሁዳ፡ የጌታ የቅርብ ዘመድ፡፡ የጸደይ (የበልግ) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 3<br>ኢያሱ ወልደ ነዌ፡፡ የክረምት (የዝናም) ወራት መግቢያ | ፳፯ 4 |
| ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>በሺ፬፻፬ ዓ.ም. የተቀባው ስመ ጥሩው ጻድቅ ኢትዮጵያዊ፡ ቀዳማዊ አጼ ቴዎድሮስ | ፴ የላስታ 7<br>ላልይበላል=ላሊበላ አብያተ ክርስቲያን፡ በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት | ማስታወሻ:- | | | |

"የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፦ 'ተነሥተህ በደቡብ በኩል፡ ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ በዳ መንገድ ኺድ!' አለው፡፡ ተነሥቶም ኼደ፡፡ እነሆም፡ ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ፥ በገንዘቧም ዅሉ የሠለጠነ፡ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፡፡ ሲመለስም፡ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን፡ 'ወደዚህ ሠረገላ ቅረብና ተገናኝ!' አለው፡፡ የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ የኾነው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ!' ስላለ፡ አጠመቀው፡፡ ከውኃው ከወጡ በኋላ፡ አቤሜሌክ፡ በተደረገለት ዕፁብ ድንቅ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም ዘለዓለማዊ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ እጅግ ተደንቆና ደስ ብሎት ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ካጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የመነጠቁን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ፡፡ የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፵፡፡

| | |
|---|---|
| የሰኔ ወር ምንባብ፦ | የሓዋርያት ሥራና ንኡሳኑ መልእክታት፡፡ |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ሐምሌ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Hamley (July-Aug., 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | ፩ 8 | ፪ 9<br>ታዴዎስ: ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ፩ዱ | ፫ 10 | ፬ 11 |
| ፭ 12<br>ቅዱሳን ሐዋርያት ጴጥሮስ ወጳውሎስ<br>የጾመ ሐዋርያት ማብቂያ፤ | ፮ 13<br>ዕርገተ እዝራ | ፯ ሥሉስ ቅዱስ: 14<br>በአብርሃም ቤት የተገኘበት::<br>በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር በሰማዕትነት የተሠዉት ፳፭ቱ የደብረ ሊባኖስ መነኰሳት | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 |
| ፲፪ 19 | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22<br>ኤፍሬም ሶርያዊ: የውዳሴ ማርያም ደራሲ | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>ነቢዩ ዮናስ ነነዌ የገባበት | ፲፰ 25<br>ያዕቆብ: የጌታ የቅርብ ዘመድና በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሊቀ ካህናትና ሰማዕት:: ኢትዮጵያውያኑ ጦብያና ጦቢት |
| ፲፱ 26<br>ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል: ሕፃኑን ሰማዕት ቂርቆስንና እናቱ ኢየሉጣን ከሚነድድባቸው የተጣሉበት ነደ እሳት ያዳነበት | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>አጼ ሠርፀ ድንግል: ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፳፪ 29<br>ዑራኤል ሊቀ መላእክት | ፳፫ 30<br>ቅዱስ ጴጥሮስ÷ ኢትዮጵያዊው ሰማዕት በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠየፈው | ፳፬ 31<br>የደብረ ሊባኖስ ገዳም በ፲፭፻፳፫ ዓ. ም. በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት÷ መነኮሳቱም፡ እየራሳቸውን በሰማዕትነት፡ በእሳቱ የሠዉበት | ፳፭ 1<br>አባ ሕፃን ሞአ ኢትዮጵያዊ |
| ፳፮ 2<br>ጻድቅ ዮሴፍ ኢትዮጵያዊ: ሕፃኑን ኢየሱስና እናቱን ለማገልገል በፈጣሪ የተመረጠ | ፳፯ 3 | ፳፰ 4 | ፳፱ 5 | ፴ 6<br>ማርያም ክብራ: (እቴጌ ናየድ ሞገሳ) የአጼ ናየድ ሚስት | ማስታወሻ:- | |

*እንግዲህ አይሁድ፡ "ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ!" ስላለ፡ ስለኢየሱስ አንጐራጐሩ፤ "ይህ ሰው፡ ሥጋውን ልንበላ÷ ደሙንም ልንጠጣ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?" ብለውም ተከራከሩ:: ከዚህ የተነሣ፡ ከደቀ መዛሙርቱ ሳይቀር፡ "ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?" ብለው ብዙዎቹ ወደኋላቸው ተመለሱ:: በዚህ ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እውነት÷ እውነት እላችኋለሁ! ሥጋዬን ካልበላችሁ÷ ደሜንም ካልጠጣችሁ፡ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም፤ ሥጋዬን የሚበላ÷ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም፡ በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ::" ሲል፡ ሊድን ለሚፈልግ፡ ለዓለሙ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ የመጨረሻ አዋጅ የኾነውን የእግዚአብሔርን እውነት ገልጦና አስረግጦ ተናገረ:: ዮሓ.፮÷ ፶፩-፶፱::*

| | |
|---|---|
| የሓምሌ ወር ምንባብ:- | ደቂቀ ነቢያት እና የዮሓንስ ወንጌል:: |

# ፪ሺ፯ (፳፻፯) ዓመተ ምሕረት ወርኀ ነሐሴ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ

2007 Era of Mercy. Month of Nehassey (Aug.-Sept., 2015). Year of Luke the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሓሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ሰንበት Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | | ፩ የፍልሰታ 7 ለማርያም ጾምና ሱባኤ መግቢያ:: ጌታን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ | ፪ 8 |
| ፫ 9 | ፬ 10 | ፭ 11 አባ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን | ፮ ማርያም 12 መግደላዊት የጌታን ትንሣኤ ቀድማ አይታ ያበሠረች | ፯ አጼ 13 ናዖድ የመልክዓ ማርያምና መልክዓ ኢየሱስ ደራሲ | ፰ 14 | ፱ 15 |
| ፲ 16 | ፲፩ 17 | ፲፪ 18 | ፲፫ ቡሔ 19 ደብረ ታቦር: ጌታ: በግርማ መለኮቱ የታየበት | ፲፬ 20 የፍልሰታ ለማርያም ሱባኤ ማብቂያ | ፲፭ 21 የፍልሰታ ለማርያም ጾም ማብቂያ፤ | ፲፮ የድንግል 22 ማርያም ትንሣኤ |
| ፲፯ 23 | ፲፰ 24 አዝማች አዳሉ በአ ሕመድ ግራኝ ወረ ራ የተሠዋ ጀግና | ፲፱ 25 | ፳ 26 | ፳፩ 27 | ፳፪ 28 | ፳፫ አባ ጊዮርጊስ 29 ዘጋሥጫ: ኢትዮጵያዊ: የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት ጸሎታት ደራሲ |
| ፳፬ 30 በ፲፪ኛው፻ ዓመት: ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት: በሰላም እንዲቀጥል ያስማማ: እጨጌ ተክለ ሃይማኖት። ክርስቶስ ሠምራ: ኢትዮጵያዊት | ፳፭ 31 | ፳፮ 1 | ፳፯ 2 አጼ ዓምደ ጽዮን: ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የተጋደለ። | ፳፰ 3 አብርሃም፥ ይስሓቅና ያዕቆብ | ፳፱ 4 ንዋየ ክርስቶስ(አለቃ ዘካርያስ) እስላሞችን: በሃይማኖት ጉባኤ የረታና ብዙዎቹን ወደክርስትና የመለሰ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ፥ ለኢትዮጵያዊነት አብ ነትና ድልድይ የኾነ። | ፴ 5 ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ: እርሱም፡ቅዱሱን ኪዳን ከኖኅ የተረከበው ፊተኛውና: አብርሃምን በባረከው በማዕከላዊው አማካይነት: ለአማናዊው መልከ ጼዴቅ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ቀዳሚ አርአያ የኾነው። |
| ጳ ጉ ሜ | | | | | | ማስታወሻ:- |
| ፩ የንስሓናሰላም 6 ለኢትዮጵያጾም መግቢያ | ፪ 7 | ፫ ሩፋኤል 8 ሊቀ መላእክት። አጼ ዘርዓ ያዕቆብ | ፬ የቅዱሳንና9 የቅዱሳት ኹሉ መታሰቢያ | ፭ 10 ነቢይ ዓሞጽ። | ፮ የንስሓናሰላም 11 ለኢትዮጵያ ጾም ማብቂያ | |

*መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል፡ ድንግል ማርያምን፡ "ደስ ይበልሽ! ጸጋ የሞላብሽ ሆይ! እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው! አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ!" አላት:: መንፈስ ቅዱስ የሞላባት ኤልሣቤጥም፡ "አንቺ፡ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ! የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው!" አለች::*

*ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ "ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ እጅግ ታልቀዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ ሐሤት ታደርጋለች፤ የአገልጋዩን መከራዋን ተመልክቷልና:: እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ 'ብፅዕት' ይሉኛል፤ ብርቱ የኾነ እርሱ፡ በእኔ፡ ታላቅ ሥራን አድርጓልና!" አለች:: ሉቃ. ፩፥ ፳፰-፶::*

| | |
|---|---|
| የነሓሴና የጳጕሜ ወራት ምንባብ:- | መጽሓፈ ጦቢትና የሉቃስ ወንጌል:: |